# የቂም ሰብል

(ከአብርሃም በየነ)

የባህሩን ጠረፍ- እንደ ዳቦ ቆርሰው፣

የምዕራቡን ድንበር - ለባዕድ አውርሰው፣

መሃሉን ዳር አርገው - ኬላውን አፍርሰው፣

ስንት አርበኛ ገድለው - ንፁህ ደም አፍስሰው፣

ድሃውን ገበሬ - አፅሙ-ርስቱን ወርሰው፣

ከቀየው ፈንግለው - ሚች ርሃብተኛ፣

አምራቹን አድርገው - ሁሉን ስደተኛ፣

ህዝቡን ጠም አዳሪ - ተመፅዋች አድርገው፣

በድህነት ህይዎት - ኩራቱን አዋርደው፣

ወኔው ተኮላሽቶ - ላገዛዝ እንዲመች፣

መብቱን አፍነው - አስረው እግር ከወርች፣

ሥርዓተ-ትምህርቱን -መሠረቱን ንደው፣

ልሂቁን በነቂስ - ካገር አሰድደው፣

ተቃዋሚውን ሃይል - እስር ቤት ጎድጉደው፣

ህዝቡን በዘር ከፍለው - እርስ-በርስ አፋጅተው፣

ቅራኔውን አርገው - እርቅ የማይፈውሰው፣

ለልጅ ልጅ የሚተርፍ - ቂም በቀል አውርሰው፣

ዕረግጠው የገዙት _ ቀንበሩን ሰባብሮ፣

ሚች ከገዳዩ ጋር - ቦታ ተቀያይሮ፣

በደም ፍላት ስሜት - ነገ ሲገናኙ፣

በቂም በቀል ባህር - በደም እንዳይዋኙ፣

እረ ተው በሏቸው - እኒያን ሰሜነኞች

አያርጉት በደሉን - ለፍርድ እንዳይመች!!!

(ጥር 2002)